# የብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና) ፕሮግራም

**(በብልጽግና ፓርቲ የመጀመሪያ ጉባኤ የፀደቀ)**

**መጋቢት 2014 ዓ.ም**
**ብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና)**
**አዲስ አበባ**

# ማውጫ


**መግቢያ** ......... 1

**ክፍል አንድ** ......... 3

I. የብልጽግና ፓርቲ ዓላማና መለያ ዕሴቶች ......... 3

1.1 የብልጽግና ፓርቲ ጥቅል ዓላማ፡- "የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ማድረግ" 4

1.2 መለያ ዕሴቶቻችን ......... 4

1.2.1 ኅብረ-ብሔራዊ አንድነት ......... 5

1.2.2 የዜጎች ክብር ......... 6

1.2.3 ነፃነት ......... 7

**ክፍል ሁለት** ......... 7

II. የፖለቲካ ፕሮግራም ......... 7

2.1 የፖለቲካ ፕሮግራም ዓላማ:- ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ዘላቂ ሀገረ-መንግስት መገንባት፣ 7

2.2 የፖለቲካ ፕሮግራም ግቦች ......... 8

2.2.1 ጠንካራና ቅቡል ሀገረ-መንግስት በጽኑ መሰረት ላይ ለመገንባት የሚያስችል ሀገራዊ መግባባት መፍጠር ......... 8

2.2.2 በተቋማዊና ህዝባዊ ባህል ላይ የቆመ የዴሞክራሲ ስርዓት መገንባት ......... 9

2.2.3 ዘላቂና አዎንታዊ ሰላምን ማረጋገጥ ......... 12

**ክፍል ሶስት** ......... 13

III. የኢኮኖሚ ፕሮግራም ......... 13

3.1 የኢኮኖሚ ፕሮግራም ዓላማ፡- ልማትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አካታች የኢኮኖሚ ስርዓት መገንባት ......... 13

3.2 የኢኮኖሚ ፕሮግራም ግቦች ......... 14

3.2.1 የብዝሃ ዘርፍ የኢኮኖሚ መዋቅር መገንባት ......... 14

3.2.2 ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ልማት እና ምርታማነትን መሰረት ያደረገ ማህበራዊ ፍትህ ማረጋገጥ ......... 17

3.2.3 ሀብት ፈጠራን የሚያሳድግ ዕውቀት-መር ኢኮኖሚ መገንባት ......... 19

3.2.4 ከተሜነት እና የከተማ ልማትን ማስፋፋት ......... 19

**ክፍል አራት** ......... 21

IV. ማህበራዊ ፕሮግራም ......... 21

4.1 የማህበራዊ ፕሮግራም ዓላማ:- ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ አካታች ማህበራዊ ልማት 21

4.2 የማህበራዊ ፕሮግራም ግቦች ......... 21

4.2.1 ፍትሃዊነት፣ ጥራት እና አግባብነት ያለው የትምህርትና ስልጠና ስርዓት ማረጋገጥ ......... 21

4.2.2 መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ስርዓት መዘርጋት ......... 23

4.2.3 የሀገራችንን አቅም ያገናዘበ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት መዘርጋት ......... 24

4.2.4 የሴቶችንና የወጣቶች የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማጎልበት ......... 25

4.2.5 ብዝሃነታችንን ማዕከል ያደረገ የቋንቋ፣ ባህልና ቅርስ ልማት ......... 25

**ክፍል አምስት** ......... 26

V. የውጭ ግንኙነት ፕሮግራም ......... 26

5.1 የውጭ ግንኙነት ዋና ዓላማ፡- ሀገራዊ ክብርን ማዕከል ያደረገ የውጭ ግንኙነት 26

5.2 የውጭ ግንኙነት ግቦች ......... 27

5.2.1 ሀገራዊ ክብርን የሚያረጋግጥ የውጭ ግንኙነት ......... 27

5.2.2 ለትብብርና ለጋራ ተጠቃሚነት ትኩረት በመስጠት አጋሮቻችንን ማስፋት ......... 28

5.2.3 የብዙዮሽ ትብብር ተቋማት ተሰሚነትን መጨመር እና ፓሊሲያዊ ነፃነትን ማስከበር ......... 28

5.2.4 ለጎረቤት ሀገራት ትኩረት በመስጠት ዘርፈ ብዙ የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ......... 29

5.2.5 የኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ተሳትፎ ማሳደግ ......... 30

5.2.6 ሀገራዊ ክብርን እና ሀገራዊ ጥቅምን የሚያስጠብቅ የውጭ ግንኙነት የመፈፀም አቅም መገንባት ......... 30

## መግቢያ

I. ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ መስኮች በርካታ አዎንታዊ ለውጦችን አስመዝግባለች። እነዚህን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ለውጦች አስጠብቆ ለማስፋት፣ ስህተቶችን ለማረም እንዲሁም የዛሬውንና የመጪውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት በዘላቂነት ለማሟላትና ሕብረብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር የኢህአዴግ አባልና አጋር ድርጅቶች ወቅቱ ለሚጠይቀው ትግል በሚመጥን መልኩ ለመደራጀት አምነው የፈፀሙትን ውህደት መነሻ በማድረግ ይህ የ "ብልጽግና ፓርቲ" ፕሮግራም ተዘጋጅቷል።

II. በሀገራችን ተጠብቀው መስፋት ያለባቸው በርካታ ድሎች ተመዝግቧል። በኢኮኖሚው መስክ ሀገራችን ለተከታታይ ዓመታት ያስመዘገበችውን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት፣ የድህነት ቅነሳ፣ የመሰረተ ልማትና የማህበራዊ አገልግሎት መስፋፋት ግለቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል። በፖለቲካው መስክ የተዘረጋው የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትን ሊያረጋግጥ የሚችል ህገ-መንግስታዊ ፌደራላዊ ስርዓት ጉድለቶቹን አርሞ መሄድን ይጠይቃል። በውጭ ግንኙነት መስክ ሀገራችን በዓለም አቀፍ መድረክ የፍትህና የገለልተኝነት ተምሳሌት መሆኗን አስጠብቀን መዝለቅ ይጠበቅብናል።

III. በሌላ በኩል ባለፉት ዓመታት የታዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስህተቶችን ያለማወላወል ማረም ያስፈልጋል። አሁን ሀገራችን በደረሰችበት የዕድገት ደረጃ ከዚህ በፊት በተከተልነው የልማት ፋይናንስ ሞዴል በኢኮኖሚና ማህበራዊ መስክ ያስመዘገብነውን ዕድገትና ልማት በተመሳሳይ መንገድ አስጠብቆ ማስቀጠል ከባድ ፈተና የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ያስመዘገብነውን የኢኮኖሚ ዕድገቱን አንድም የዕድገት ምንጮችን በማስፋት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመንግስት ጉድለት ምክንያት የተፈጠረውን የሀገር ሀብት ብክነትና ዝርፊያ በመከላከል፣ የሀገራችንን ህዝቦች ፍትሃዊና የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በመሆኑም ምርታማነትን የሚያሳድግና በግሉ ባለሀብትና በመንግስት ትብብር የሚገነባ የኢኮኖሚ ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። የግሉ ባለሀብት በሀገራችን ውስጥ በቂ ሀብት የሚፈጥርበትንና ምርታማነት የሚያድግበትን የፋይናንስ ሞዴል መከተል ይጠይቃል።

በፖለቲካው መስክ የብሔር ማንነትን እና ሀገራዊ ማንነትን፣ አጣጥሞ በዘላቂነት የሚያስኬድ የሀገርና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ማካሄድ ያስፈልጋል።

ህብረተሰብን በጎራ በመከፋፈል አግላይ የነበረው አካሄድና አደረጃጀት አቃፊና አካታች ሆኖ የሀገራችንን ተጨባጭ የፖለቲካ ችግር በሚፈታ ማእቀፍ ሊሻሻል ይገባል። የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዕንቅፋት የሆኑ ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች ከዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች የላቁ ናቸው የሚለው ምሉዕነት የጎደለው ትንተናና የፖለቲካ ፕሮግራም፣ ሀገራዊ ሁለንተናዊ ብልጽግናን በሚያስቀድሙ የፖለቲካ ዕይታዎች መተካት ይኖርበታል። የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲያችን መቀጨጭ ታርሞ ግልጽና ለሁሉም የሀገራችን ህዝቦች የዴሞክራሲ ስርዓት ማሳያ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል።

IV. ሀገራችን ኢትዮጵያን የአሁኑንና የመጪውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት የሚያስከብር አስተማማኝ መሰረት ዛሬ ላይ በመገንባት ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ ህብረ ብሄራዊ አንድነት፣ የዜጎች ክብር፣ ፍትህ እና የጋራ ብልጽግና የተረጋገጠባት ሀገር መሆን ይኖርባታል። ኢህአዴግ በትጥቅ ትግል ለድል ከበቃ በኋላ ለ28 ዓመታት ሀገርን በመራበት ታሪኩ የተንቀሳቀሰበት ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ አውድ ተለውጧል። በተያያዘም ኢህአዴግና አጋር ድርጅቶች ሲከተላቸው የነበሩ የርዕዮተ ዓለም ዕሳቤዎች ፖለቲካዊ አዋጭነታቸው መንምኗል። ፓርቲያችን ከዘመናዊ የፖለቲካ ጨዋታ ህግጋት ጋር ተናቦ የሚሄድ የዕይታ ለውጥ በአጭር ጊዜ በማካሄድ እየተለወጠ ካለው ምህዳር ጋር መዋጀት እና እንደ ሀገርም ከፍተኛ ጥፋትን ሊያስከትል ከሚችል የቆሞ ቀርነት አዙሪት ውስጥ መውጣት ወሳኝ ነው።

V. በጥቅሉ ሀገራችን በኢህአዴግ አመራር በቆየችባቸው ዓመታት የነበሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ድሎችን ጠብቆ ማስፋት፣ ጉድለቶችን ነቅሶ በማውጣት ያለማወላወል እንዲታረሙ ማድረግ እና የዛሬውንና የመጪውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት ማሟላት ያስፈልጋል። ሆኖም ግን በቀድሞ ኢህአዴግና አጋር ድርጅቶች ቅርጽና ይዘት እነዚህን ድሎች ጠብቆ ማስፋት፣ ስህተቶችን ማረም እና የመጭውን ትውልድ ጥቅም የማስከበር አላማዎችን በተሟላ መልኩ ማሳካት አይቻልም። በመሆኑም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችን እና አጋር በሚል ሲጠሩ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማካተት፣ አቃፊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርዓት የሚገነባ **"የብልጽግና ፓርቲ"** የሚሰኝ ህብረ-ብሔራዊ ፓርቲ ማቋቋም አስፈልጓል።

VI. ወጥ ዓላማ ያለው ህብረ-ብሔራዊ ውህድ ፓርቲ መሆን ሰፊውን የሀገራችንን የህዝብ ክፍል የሚያቅፉ ነገር ግን በዕይታ ግድፈት ከሀገራዊ የፖለቲካ ውሳኔ የተገለሉትን ኢትዮጵያዊያን በእኩልነት የሚሳተፉበትን ፓርቲያዊ አወቃቀር

ለማምጣት ያስችላል። በሌላ በኩል ህብረ-ብሔራዊ ፓርቲው አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ብሔሮች በሚያሳትፍ እና በሚያካትት መልኩ ውክልና እና ብቃትን መሰረት ያደረገ የውሳኔ አሰጣጥ ትስስሮሽን በማጠናከር በሃሳብ ልዕልና ላይ የተመሰረተ ዘመናዊ የፖለቲካ ፉክክርና ትብብር መሰረት እንዲይዝ በማድረግ ሀገራችን የተያያዘችው ዴሞክራሲያዊ የለውጥ ሂደት ቀጣይነት ኖሮት ከማይቀለበስበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ እና እንዲጠናከር የሚያግዝ ይሆናል። በአጠቃላይ እውነተኛ ህብረ-ብሔራዊ የሆነው ውህድ ፓርቲያችን የአላማና የተግባር ውህደት በማምጣትና የተሻለ ኃይል በማሰባሰብ በቀጣይ ለላቀ የዓላማ አንድነትና ሀገራዊ ድል የሚያበቃ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ አቅጣጫ የሚከተል ይሆናል።

# ክፍል አንድ

## I. የብልጽግና ፓርቲ ዓላማና መለያ ዕሴቶች

ፓርቲያችን ሀገራችንን የሚመለከትበት የዕይታ ማዕቀፍ በጥቅሉ የነበረውን ጠንካራ መሰረት በማስጠበቅ እና ውስንነቶችን በማረም ሁለንተናዊ የብልጽግና ምዕራፍ መክፈት የሚል ነው። ይህን የዕይታ ማዕቀፍ በተጨባጭ ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ በተለያዩ ቡድኖች፣ መደቦች፣ ማንነቶች፣ ወዘተ የሚስተዋሉ ዋልታ-ረገጥ አስተሳሰቦች ሚዛን ጠብቀው እንዲሄዱ ያደርጋል። በዚህም ምክንያት ከወግ አጥባቂ ዝንባሌዎችም ሆነ አፍርሰው ከሚገነቡ አስተሳሰቦች ይልቅ የሀገራችንን ተጨባጭ ችግሮች የሚፈታ፣ ህዝቡን የሚጠቅም፣ በመግባባትና በውጤት ላይ የሚያተኩር እንዲሁም ከርዕዮተ ዓለም ጥገኝነትና እስረኝነት የተላቀቀ የመካከለኛው መንገድን ተመራጭ ያደርጋል።

በሀገራችን የቀኝ እና የግራ አሰላለፍ ልማድ በመሰረቱ ከመደባዊ ውግንናና ዝንባሌ ይልቅ አጠቃላይ በሀገረ-መንግስቱ ዙሪያ ባሉ ዕይታዎች ላይ የሚያጠነጥን መሆኑን በመረዳት እነዚህን አመለካከቶች የሚያቀራርብ አሰላለፍን ይከተላል። ይህ አተያይ ሁኔታዎችን ቋሚ አድርጎ ከመመልከት ይልቅ ነባራዊ እውነታን እያነበበ፣ ቋሚ መርሆችን ማዕከል አድርጎ ጉዞን የመፈተሽ እና በጥናት ላይ እየተመሰረተ የሚቀጥል መርህ-ተኮር የተግባራዊነት ዕሳቤን ይከተላል። በዚህም ምክንያት ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የሚያሰባስብና የፓርቲው ማህበራዊ መሰረት ማድረግ የሚያስችል አካታች ፖለቲካዊ ጉዞን ተመራጭ ያደርጋል። ፓርቲያችን **"ሀገራችን ለሁላችንም ትበቃለች"** የሚል ጽኑ ሃሳብ በመያዝና የዕጦት አስተሳሰብን በመሻገር ለሁሉም ዜጎች

የምትሆንና ሁሉም በኩራትና በምቾት የሚኖርባት የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ትግል ያደርጋል። ይህንን ዓላማ የሚፃረሩ በግራም ሆነ በቀኝ የተሰለፉ አፍራሽ አስተሳሰቦችንና ተግባሮችን ሁሉ ፓርቲያችን በጽኑ ይታገላል።

## 1.1 የብልጽግና ፓርቲ ጥቅል ዓላማ፦ "የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ማድረግ"

የፓርቲያችን ጥቅል ዓላማ የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነው። ብልጽግና ስንል ፈርጀ ብዙ ትርጓሜን አዝሎ የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ እና ማህበራዊ ገጽታ ያለው ነው። የኢኮኖሚ ብልጽግና፣ የህዝቦች መሰረታዊ ፍላጎቶች በተገቢና በዘላቂነት ለማሟላት ፈጣን እና ሁለንተናዊ ዕድገትን በማስመዝገብና ዓለም-አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ያለው ኢኮኖሚ በመገንባት ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥና የህዝቦችን ድህነትና ኋላ-ቀርነትን ለመቅረፍ መቻልን ያካተተ ነው። የፖለቲካ ብልጽግና ስንል ለዴሞክራሲ ባህል ማበብ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን በመገንባት፣ የህዝቦች ነፃነትና እኩልነት ተረጋግጦ፣ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ተከብረውላቸው የሚኖሩባት፣ ህብረ-ብሔራዊ አንድነቷ የተረጋገጠ፣ ፌዴራላዊት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ጽኑ መሰረት ላይ ማቆም ማለታችን ነው። ማህበራዊ ብልጽግና መልካም ሀገራዊ ወጎችን፣ ዕሴቶችን እና ባህሎችን በማዳበር በስነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ማፍራት፣ በአካልና በአእምሮው የዳበረ ጤናማ ዜጋ መፍጠር፣ ከአስከፊ ማህበራዊ ችግር የተጠበቀ ህብረተሰብ መገንባት እና በህዝቦች መካከል አዎንታዊ ሰላም በመፍጠር ሁለንተናዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ ማለት ነው።

## 1.2 መለያ ዕሴቶቻችን

ዕሴቶቻችን ቅድሚያ ዋጋ የምንሰጣቸውና የምንታገልላቸው ወደ ብልጽግና ዓላማ የመድረሻ መንገዳችን አመልካቾች ናቸው። በምንጓዝበት መንገድ ሁሉ በሚገጥሙን የተለያዩ አጣብቂኞች ቅድሚያ የምንሰጠው የዜጎችና የሕዝቦች ክብር፣ ነፃነት፣ ፍትሕ፣ ኅብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትና እኅትማማችነት፣ መከባበርና መቻቻል፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ አሳታፊነት ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ይሆናሉ። ለአብነትም መለያ እሴቶቻችን እንደሚከተለው ተብራርቷል፡፡

### 1.2.1 ኅብረ-ብሔራዊ አንድነት

የፓርቲያችን ዋነኛ ዓላማ ህብረ-ብሔራዊነቱ የተጠበቀ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መገንባት ነው። ህብረ-ብሔራዊ ስንል የብሔር፣ የሃይማኖት ወይም ሌላ ማንነቶችን ያቀፈና ማንንም ያላገለለ ማህበረሰብ ማለታችን ነው። የፓርቲያችን ህብረ-ብሔራዊነት በሁሉ-አቀፍነት፣ በብዝኃ-ልሳንነት እና በአሳታፊነት ሊገለጽ ይገባል ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። ህብረ-ብሔራዊ አንድነት ብዝኃነትን እንደጸጋ የሚመለከት ለሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዕውቅና የሚሰጥና ካላቸው የታሪክ ትስስር፣ ተመሳሳይ አሁናዊ ሁኔታ፣ የጋራ ጥቅም እና ተስፋ በመነሣት ጠንካራ ህብረትና ትብብር ሊኖራቸው ይገባል የሚል ዕሴት ነው።

ህብረ-ብሔራዊ አንድነት፣ ማንነታችን እርስ በርሱ የተጋመደ፣ የተሰናሰለ እና የተዋሃደ መሆኑን አመላካች ነው። ህብረ-ብሔራዊ አንድነት፣ ዕጣ ፈንታችን እጅጉን የተቆራኘ መሆኑን በመገንዘብ ለጋራ ዓላማና ግብ አብረን መቆም፣ አብረን መስራት፣ መደጋገፍ እና መተጋገዝ እንደሚገባን የሚያስገነዝብ አመለካከት ነው። ህብረ-ብሔራዊ፣ አንድነት ታሪካዊና ነባራዊ በደሎች ከማድበስበስ ይልቅ ታርመው እንዲሄዱ፣ ይህም ለቁርሾ ሳይሆን ወዳጅነትን ለማጠናከር እንዲውል የሚያደርግ አካሄድ ነው። ህብረ-ብሔራዊ አንድነት፣ የሚከፋፍሉ እና የሚያጣሉ ትርክቶችን ከማጉላት ይልቅ የሚያቀራርቡና የሚያስተሳስሩንን እውነታዎች በማጉላት፣ ከትናንት ጠቃሚ ትምህርቶችን በመውሰድ እንዲሁም ዛሬና ነገ ላይ በማተኮር እህታዊ/ወንድማዊ ህብረትን በብሔሮች መካከል ማጠናከርን ይመርጣል። ህብረ-ብሔራዊ አንድነት ብዙ ሆነን አንድ፣ አንድ ሆነንም ብዙ የምንሆንበት፣ ለጋራ ግብና ዓላማ የምንደመርበት ቀመር ነው። በብዝኃነታችን ደምቀን፣ በአንድነታችን በርትተን ወደፊት የምንራመድበት የውበትና የጥንካሬያችን ምንጭ ነው።

ፍትህ ከሰፈነ፣ ሰብአዊ ክብር ከጎለበተ እና ብልጽግና ከመጣ እንደ ሀገር የመቀጠል ተስፋችን ይለመልማል። ሆኖም ግን ህብረ-ብሔራዊ አብሮነት እነዚህ ምሰሶዎች ከተሳኩ በኋላ የሚመጣ ብቻ ሳይሆን ለዓላማዎች ስኬትም ዓይነተኛ ድርሻ የሚወጣ አስቻይ አቅም በመሆኑ ፓርቲያችን **"በህብረት ሆነን እንበለጽጋለን፤ በልጽገንም በህብረት እንኖራለን"** በሚል መርህ ህብረ-ብሔራዊ አንድነትን ለማረጋገጥ በከፍተኛ ትኩረት ይሰራል።

### 1.2.2 የዜጎች ክብር

የዜጎች ክብር ስንል ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ልታስጠብቅላቸው የሚገቡ በዜግነታቸው ሊያገኙ የሚገባቸውን ክብር እና በሀገራቸው ለመመካት የሚያስችላቸውን ሁኔታ ማለታችን ነው። የብልጽግና ፓርቲ ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ ሊከበር ይገባል ብሎ ያምናል። ዜጋ ሃይማኖቱ፣ ብሔሩ ወይም ጾታው ብሎም ሀብቱና ድህነቱ ከግምት ሳይገባ መሰረታዊ ፍላጎቱ ሊከበርለት፣ በእኩል ዓይን ሊታይ እና ፍትህን ሊያገኝ ይገባል ብለን እናምናለን። በመሆኑም የዜጎች ክብር ስንል በሀገራችን ማንኛውም ቡድን ወይም ግለሰብ ከሌሎች የተለየ ተጠቃሚ አሊያ ተጎጂ እንዳይሆን መስራት ማለታችን ነው። የዜጎች ክብር ስንል ኢትዮጵያውያንን በእኩል ዓይን የሚያይና የሚዳኝ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በህግ ፊትና በሀገራችን በእኩል የሚታዩበትና በፍትሃዊ መልኩ ተጠቃሚ የሚሆኑበት፣ የብዙሃንም ሆነ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሔሮች መብትና ነፃነት የሚከበርበት፣ ሰው በሰውነቱ በእኩል የሚታይበት፣ ከበደልና ጭቆና ነፃ የሚሆንበት፣ በዋና ዋና የሀገሪቱ ጉዳዮች ላይ ሁሉም ዜጋ በውሳኔ ላይ ተሳታፊ የሚሆንበት እንዲሁም የሀብት፣ የስልጣንና የመብት ክፍፍሉ ርዕታዊና አግባብ፣ ለህሊና የማይቆረቁር የሆነበት የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ስርዓት መፍጠር ማለታችን ነው።

የዜጎች ክብር፣ የግለሰብና የቡድኖች እኩልነት እና የሀገር ሉዓላዊነትን አቅፎ በግለሰብ፣ በማህበረሰብ እና በሀገር ደረጃ የሚታይ ነው። ማህበረሰባዊና ሀገራዊ ክብር ህዝቦች በሀገራቸውም ሆነ በዓለም መድረክ ቀና ብለው ለመሄድ መቻል ነው። ይህ የብዙ ነገሮች ድምር ውጤት ነው። በዋነኝነት በሀገር ውስጥ የፍትህና የብልጽግና ጥያቄዎችን በመመለስ እንዲሁም ከሀገር ውጭ የኢትዮጵያውያንን ደህንነትና መብት በማስከበር ኢትዮጵያውያን በሀገራቸውና በማህበረሰባቸው ክብር እንዲሰማቸው ማድረግ ማለት ነው። በተመሳሳይም ደግሞ በዓለም መድረክ ስሟ በበጎ የሚነሳ ሀገር በመገንባት የህዝባችንን ክብር ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል። በዜግነት ክብር የሀገራችንን ስም ከፍ ማድረግ፤ ከፍ ያለች ሀገር በመገንባት ደግሞ የዜግነት ክብርን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ተመጋጋቢነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው።

በመሆኑም ፓርቲያችን በሀገራችን የህግ የበላይነትን በማስፈን፣ ሃቀኛ የፍትህ ስርዓት በመገንባት፣ መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶችን በማክበር፣ ማህበራዊ ፍትህን በማረጋገጥ፣ የማህበረሰባችንን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅ፣ ሰዎችን የሚያስቀድም የኢኮኖሚ ዕድገትን በማሳለጥና ሁሉን አቀፍ ብልጽግናን በማምጣት ሰብአዊ፣ ማህበረሰባዊ እና ሀገራዊ ክብርን ለማስጠበቅ ይታገላል።

### 1.2.3 ነፃነት

ከፓርቲያችን ዕሴቶች አንዱ ዜጎች የራሳቸውን የህይወት ርዕይ የመምረጥና በመረጡት መንገድም የመኖር መብታቸው እንዲረጋገጥላቸው ማድረግ ነው። ማህበራዊ ዕሴቶችንና ጥቅሞችን ማስጠበቅ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ሰው ሀሳቡን በነፃነት እንዲገልጽ፣ የፈለገውን እምነት እንዲከተል፣ ከፈለገው ጋር እንዲሰባሰብና እንዲደራጅ ነፃነት ካላገኘ ብቁና መልካም ህብረተሰብ ሊፈጠር አይችልም ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። በግድና በጉልበት እነዚህ  ነፃነቶቹ ተገድበውበት የሚኖር ህብረተሰብ ምንም እንኳን ቁሳዊ ፍላጎቶቹ ቢሟሉም ቁሳዊ ያልሆነው ማንነቱ ግን ችግር ውስጥ እንዳለ መረዳት አስፈላጊ ነው ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። ነፃነትን ማረጋገጥ ያልቻለ ስርዓት በአንድ በኩል ዜጎችን ንቁና ምርታማ እንዳይሆኑ የሚያደርግ፣ ሀብት ፈጠራን የሚገድል እና በጥቅሉም የብልጽግና ጉዞን የሚኮደኩድ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን ሲፈጥር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቁርሾና ብሶትን የሚያቀጣጥል፣ የሃሳብ ልውውጥን የሚያሳሳ እና ፍርሃትን የሚያነግስ የፖለቲካ ድባብን ይፈጥራል። በመሆኑም ፓርቲያችን የሀገራችንን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታትና የዜጎችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማሳደግ ይቻል ዘንድ ነፃነትን አንዱ ዕሴቱ አድርጎ ይንቀሳቀሳል።

# ክፍል ሁለት

## II. የፖለቲካ ፕሮግራም

### 2.1 የፖለቲካ ፕሮግራም ዓላማ:- ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ዘላቂ ሀገረ-መንግስት መገንባት፣

የብልጽግና ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራም ዋነኛ ዓላማ ጠንካራና ቅቡልነት ያለው፣ የብሔር ማንነትን እና የሀገራዊ አንድነትን ሚዛን የጠበቀ ሀገረ-መንግስት መገንባት ነው። ከጠንካራ ሀገረ-መንግስት ግንባታ አንፃር ፓርቲያችን ህዝብ ከቀጥተኛ የህልውና አደጋ ተጠብቆ የልማት፣ የእኩልነት እና የነፃነት ፍላጎቶቹ እንዲሟላለት የሚያስችል ነፃ፣ ገለልተኛና ብቃትን መሰረት ያደረገ ሀገራዊ ተቋማዊ አደረጃጀት መገንባት ያስፈልጋል ብሎ ያምናል። በመሆኑም የሀገረ-መንግስት ግንባታ ጅምራችን ጠንካራና የማይናወጥ ተቋማዊ መሰረት ያለው እንዲሆን የብልጽግና ፓርቲ ግቡ አድርጎ ይንቀሳቀሳል። የብልጽግና ፓርቲ ዴሞክራሲን በተቋማዊና ህዝባዊ ባህል ላይ መገንባት አስፈላጊ እንደሆነ ይገነዘባል። በሌላ በኩል ከሀገረ-መንግስት ቅቡልነት አንፃር የብልጽግና ፓርቲ የኢትዮጵያ ሀገረ-መንግስት ጥንካሬን ለማሳደግ በህገ-መንግስታችን የተቀመጠውን አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር ግብ

ለማሳካት ይሰራል። በመሆኑም የሀገረ-መንግስቱን ቅቡልነት በሚጨምሩና ሀገራዊ መግባባትን በሚያመጡ፣ የህዝቦችን ግንኙነት በሚያሳልጡ እና የእውነተኛ ዕርቅ መንፈስን በሚያጎለብቱ ፖለቲካዊ እርምጃዎች ላይ ትኩረት አድርጎ ይንቀሳቀሳል። ፓርቲያችን የሀገረ-መንግስት ግንባታችን ህብረ-ብሔራዊ ማንነትን የተላበሰና ብዝሃነትን የሚያንፀባርቅ መሆን እንዳለበት በጽኑ ያምናል።

## 2.2 የፖለቲካ ፕሮግራም ግቦች

### 2.2.1 ጠንካራና ቅቡል ሀገረ-መንግስት በጽኑ መሰረት ላይ ለመገንባት የሚያስችል ሀገራዊ መግባባት መፍጠር

2.2.1.1 የብልጽግና ፓርቲ የቆመላቸው የፖለቲካ ዓላማዎች እንዲሳኩ ፓርቲው ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራባቸው ነገሮች አንዱ የሀገራዊ መግባባት ጉዳይ ነው። ህብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን ለማጠናከር፣ ለዴሞክራሲ ስርዓቱ ምቹ መደላድል እንዲኖር ለማድረግ፣ የሀገረ-መንግስቱን ቅቡልነትም ከፍ ለማድረግ የብልጽግና ፓርቲ ሀገራዊ መግባባትን ለማዳበር በጽኑ ይሰራል።

2.2.1.2 የብልጽግና ፓርቲ በሀገሪቱ ልሂቃን መካከል የሚታየው ዋልታ-ረገጥነት እና እጅግ መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ሳይቀር ያለው ቅራኔና አለመተማመን ጤናማ እንዳልሆነ ይገነዘባል። ፓርቲው የሃሳብ ልዩነቶች እንዲሁም የጥቅምና የፍላጎት አለመጣጣሞች ተፈጥሯዊ መሆናቸውን ይረዳል። እንደዚህ ያሉ ልዩነቶች አይቀሬና በዴሞክራሲ አግባብ ሊስተናገዱ ቢችሉ ጠቃሚና ገንቢ ናቸው ብሎም ያምናል። ነገር ግን ሀገራዊ ህልውናን እና ህብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን አጠያያቂ የሚያደርጉ፣ የሀገረ መንግስቱን ቅቡልነት የሚሸረሽሩ የከረሩ አለመግባባቶች ግን አሉታዊ ተጽዕኗቸው ከፍ ያለ እንደሆነ ይገነዘባል። በመሆኑም የብልጽግና ፓርቲ እጅግ መሰረታዊ በሆኑና ለሀገረ-መንግስቱ ቅቡልነት ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሰፊና ጠንካራ ሀገራዊ መግባባት እንዲዳብር ይሰራል።

2.2.1.3 ፓርቲያችን ሀገራዊ መግባባትን ለማዳበር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ቅድሚያ ሰጥቶ ከሚሰራቸው ተግባራት አንዱ በሀገራችን የቂምና የጥላቻ ታሪክ ምዕራፍ እንዲዘጋ ማድረግ ነው። ይህን ለማሳካት ባህላዊና

ዘመናዊ የዕርቀ ሰላም ግንባታ አማራጮችን በመጠቀም ዕርቀ ሰላምን ለማምጣት በቁርጠኝነት ይታገላል። ለቀጣዩ ትውልድ ቂምና ቁርሾ ሳይሆን ሰላም፣ ወንድማማችነትንና እህትማማችነትን ለማውረስ የዕርቀ ሰላም አማራጮችን ሁሉ አሟጦ ይጠቀማል።

2.2.1.4 የሃሳብ ልዩነቶችን ለማጥበብ እና ቅራኔዎችን ለማስወገድ ፓርቲያችን በጥናት ላይ የተመሰረተ ውይይቶችን እና ህዝባዊ ተዋስኦዎችን የሚያስቀድሙ ድርድሮችን በተከታታይና በቀጣይነት እንዲካሄዱ በማድረግ ሀገራዊ መግባባትን ለማዳበር ይሰራል። በነጠላ ጉዳዮች ላይ የጠለቁ ውይይቶች እንዲካሄዱ በማድረግ ቅራኔዎችን ደረጃ በደረጃ እየፈቱ ለመሄድ በትጋት ይንቀሳቀሳል።

2.2.1.5 የብልጽግና ፓርቲ በሀገራችን የምንፈጥረው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ህብረ-ብሔራዊ አንድነትን የጠበቀና የሁሉም ማንነቶች ነፀብራቅ የሆነ፤ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ባህልና ማንነት የጠበቀ መሆን እንዳለበት በጽኑ ያምናል። ስለሆነም የምንገነባው ማህበረሰብ ህብረ-ብሔራዊና በአጠቃላይም ህብረ-ማንነታዊ እንዲሆን፣ ዜጎችም ብዝሃነትን የተረዱና የሚያከብሩ እንዲሆኑ አበክሮ ይሰራል።

## 2.2.2 በተቋማዊና ህዝባዊ ባህል ላይ የቆመ የዴሞክራሲ ስርዓት መገንባት

2.2.2.1 የብልጽግና ፓርቲ የበለፀገችና ህብረ-ብሔራዊ አንድነቷ የተረጋገጠ ኢትዮጵያን ያለ ዴሞክራሲ እውን ማድረግ አይቻልም ብሎ ያምናል። የህዝቦች ድምር የልማት፣ የእኩልነት እና የነፃነት ፍላጎት የሚያሟላ ሁለገብ የሆነ ብልጽግና እንዲመጣ የዴሞክራሲ አጀንዳ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ፓርቲያችን የህዝብ ሉዓላዊነት መከበር እንዳለበትና የመንግስት ስልጣን በህዝብ ይሁንታና ውክልና በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ብቻ ሊገኝ እንደሚገባ ያምናል። ዴሞክራሲ የህዝብ ወኪሎች ከሚመረጡበት የምርጫ ሂደት አልፎ በይዘቱም የህዝቦች እኩልነት፣ ነፃነት እና ውክልና የሚረጋገጥበት እንዲሆን ይታገላል። የብልጽግና ፓርቲ ዴሞክራሲ በትምህርት፣ በጤና፣ በመሰረተ ልማት ግንባታ በመታጀብ አሰላሳይ፣ ሞጋችና ፈጣሪ ህብረተሰብ በመገንባት ረገድ አስተዋጽኦ ሊኖረው ይገባል ብሎ ያምናል። በመሆኑም የምንገነባው ዴሞክራሲ ተቋማዊ መሰረቱ ጽኑ

እንዲሆንና ዴሞክራሲያዊ ዕሴቶች የዳበሩ እንዲሆኑ ብሎም ወደ ባህልነት ደረጃ እንዲያድጉ ፓርቲያችን ይሰራል። በሀገራችን አስተማማኝና ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ተመስርቷል ልንል የምንችለው የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በአስተማማኝና በጠንካራ ተቋማዊ እና ዴሞክራሲያዊ ባህል መሰረት ላይ ሲታነጽ እና ስርዓቱ ራሱን እያጠነከረ መደበኛ ሂደት ውስጥ በመግባት የማይቀለበስበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። ይህ የማይቀለበስ የዴሞክራሲ ጉዞ ብዙ ዓመታትን ሊፈጅ የሚችልና በመሰናክሎችም የታጀበ ውጣ ውረድ ያለው መሆኑን በመገንዘብ ፓርቲያችን ጽኑ ትግል ያደርጋል።

2.2.2.2 የምንገነባው የሴሞክራሲ ስርዓት የግለሰብ መብቶችንና የቡድን መብቶችን ሳያበላልጥ የሚያስከብርና ሁለቱንም የመብት ዓይነቶች ለማስከበር በየባህሪያቸው ልክ የተቀየሰ አቅጣጫን ይከተላል። ፓርቲያችን የግለሰብና የቡድን መብት ተነጣጥለው ሊሄዱ እንደማይችሉ ይገነዘባል። የግለሰብ መብትን በተሟላ መልክ ለማክበር ለቡድን መብቶችም እኩል ዕውቅና እና ትኩረት መስጠት እንደሚገባ፣ እንዲሁም የቡድን መብቶች በተሟላ ሁኔታ እንዲከበሩ ለማድረግ የግለሰብ መብቶችን ማክበር አስፈላጊ እንደሆነ ፓርቲያችን ያምናል። ይህን እውን ለማድረግም ፓርቲያችን እውነተኛ፣ ዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ስርዓት ለማጠናከር በጽኑ ይታገላል። ፓርቲያችን የፌደራል ስርዓቱ ዋና ምሰሶ ብዝሃነትን ለማስተናገድ እና ህብረ-ብሔራዊ አንድነትን ማጠናከር መቻሉ ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም ለብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዕውቅና የሰጠ ፌዴራላዊ ስርዓት በመገንባት ኢትዮጵያ የብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መብት የተከበረባት እውነተኛ ህብረ-ብሔራዊት ሀገር እንድትሆን ይሰራል። በአንፃሩም የግለሰብ መብቶችን በተመሳሳይ በህገ-መንግስት ማዕቀፍ ስር ማስከበር ይቻላል ብሎ ያምናል።

2.2.2.3 እንደ ኢትዮጵያ ብዝሃነት በሚንፀባረቅባቸው ሀገራት በፉክክር ላይ ብቻ የተመሰረተ ሳይሆን የትብብር እና የፉክክር ሚዛንን የጠበቀ የዴሞክራሲ ስርዓት ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ፓርቲያችን ያምናል። ስለዚህ ፓርቲያችን ለትብብርና መግባባት ትኩረት የሚሰጥ የስልጣን ክፍፍልና ውክልና፣ እራስን በራስ የማስተዳደር ያልተማከለ ፌደራላዊ ስርዓት እና ታላቅ ቅንጅትን መሰረት ያደረገ የጋራ አስተዳደር እንዲሁም ትንሽ ቁጥር ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች መብት በልዩ ሁኔታ የሚያስከብር

አካታችና የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲገነባ በማድረግ በሂደት በሃሳብ ልዕልና ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ይታገላል።

2.2.2.4 ብልጽግናን ማረጋገጥ እና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ውጥን ያለ ነፃ፣ ገለልተኛ እና ሙያዊ ብቃት ያዳበሩ ተቋማት እውን ሊሆን እንደማይችል ፓርቲያችን በጽኑ ያምናል። ስለሆነም የዴሞክራሲ ግንባታ ስራዎቻችን ለተቋማት ግንባታና አሰራር ቅድሚያ የሚሰጡና በዚያ ዙሪያ የሚያተኩሩ ይሆናሉ። ስለዚህም ፓርቲያችን የህዝብ አስተዳደር፣ የዴሞክራሲ፣ የሰላም እና የደህንነት እንዲሁም የህግ አስከባሪና የፍትህ ተቋማት እንደየ ባህሪያቸው ነፃ፣ ገለልተኛ እና ብቃት ያላቸው እንዲሆኑ በትጋት ይሰራል። የመንግስትና የፓርቲ አሰራሮች በሀገራችን የመደበላለቅ መሰረታዊ ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ ፓርቲያችን ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል።

2.2.2.5 ፓርቲያችን የፀጥታና የደህንነት ተቋማት በዴሞክራሲያዊ መሰረት ላይ የታነፁ ነፃ፣ ገለልተኛ እና ለሀገር እና ለህዝብ ጥቅም የቆሙ ወገንተኝነታቸው ለሀገር ብቻ የሆኑ ተቋማት ለማድረግ ይታገላል። በዚህም ረገድ በየተቋማቱ ያለውን የሙያ ብቃት እና ክህሎት፣ እንዲሁም አደረጃጀት ከአካባቢው ሁኔታ እና ከዘመናችን የቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር አቆራኝቶ ተቋማቱን ለማጠናከር በትኩረት ይሰራል።

2.2.2.6 የሀገረ-መንግስቱን ጥንካሬ ለማጎልበት እንዲሁም ተቋማት የተጣለባቸውን ህዝባዊ አደራ እና ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ሀገረ-መንግስቱ የተዋቀረባቸው ተቋማት ባህሪ እና ተልዕኮን ማዕከል ያደረገ፣ በዕውቀት የሚመራ፣ የየዘርፉን ልዩ ባህሪ ያገናዘበ፣ ለአመራር ብቃት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ያልተማከለ የተቋማት ሪፎርም እንቅስቃሴ ፓርቲያችን ተግባራዊ ያደርጋል።

2.2.2.7 ፓርቲያችን ማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ርዕዮተ ዓለማዊ፣ ህጋዊ ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎች ሁሉ ህገ-መንግስትን የተከተሉ መሆን አለባቸው ብሎ ያምናል። የህግ አውጭው፣ የህግ አስፈፃሚው እና የህግ ተርጓሚው የስልጣን ክፍፍል በአግባቡ ተፈፃሚ እንዲሆንና የእርስ በርስ ቁጥጥርና ሚዛን እንዲጠናከር፣ የመንግስት አካላት ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ፣ ህግ አውጭውን የሚያጠናክሩና የዳኝነት አስተዳደሩን የሚያጎለብቱ አሰራሮች እንዲዘረጉ ያደርጋል። ፓርቲያችን ህገ-መንግስቱ መሻሻል ያለበት ህዝብን

ባሳተፈ እና ህገ-መንግስቱ ራሱ ባስቀመጠው መንገድ ህግና ስርዓት በተከተለ አካሄድ ብቻ መሆን አለበት ብሎ ያምናል።

2.2.2.8 ፓርቲያችን በፌዴራል ስርዓቱ በማንኛውም ጊዜ የሚነሱ የማንነትና የወሰን ጥያቄዎች ህጋዊ፣ ሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ በሆነ እንዲሁም የህዝቦችን አብሮነት፣ ወንድማማችነትና እህትማማችነት በሚያጠናክር መልኩ እንዲፈቱ ይታገላል።

2.2.2.9 የብልጽግና ፓርቲ በዚህ ፕሮግራም የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የመንግስት ተቋማትን የማስፈፀም አቅም ለማሳደግ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል። የፓርቲውን ፕሮግራም ለማሳካት ዕንቅፋት የሚሆኑ፣ የሀገር እና የህዝብን ጥቅም የሚጎዱ ከህሊና ቢስነት የሚመነጩ ብልሹ አሰራሮችን፣ ልግመኝነትን እና በተለይም የተደራጀ ሌብነትን በጽኑ ይታገላል። የህግ የበላይነትንና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ፣ የተደራጀ ሌብነትን ከምንጩ ለማድረቅ ይሰራል። የሀገራችን ዜጎች ለፍተው በስራ እና በጥረታቸው ሀብት የሚያፈሩባት እንድትሆን ፓርቲያችን ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ጠንክሮ የሚሰራውን ያህል፣ ህዝብን እና ሀገርን በሚጎዳ አቋራጭ መንገድ ወይም በሌብነት ሀብት ለማግኘት የሚፈልጉትን ደግሞ በጽናት በመታገል፣ ማህበረሰባችን የግብረ-ገብ ውሃ ልኩን ጠብቆ እንዲጓዝ ይታገላል።

## 2.2.3 ዘላቂና አዎንታዊ ሰላምን ማረጋገጥ

2.2.3.1 ፓርቲያችን ሀገራችን ህልውናዋ ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ትቀጥል ዘንድ ሰላሟ ሊጠበቅላት ይገባል ብሎ ያምናል። በመሆኑም ማህበራዊ ሀብቶቻችንን በመጠቀም ህዝብና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍና በማስተባበር የሰላም ባህል በመገንባት፣ የህግ የበላይነትን በማስከበርና ፍትህን በማስፈን እንዲሁም ሀገራዊ መግባባትን በማጎልበት ፓርቲያችን ግጭትን ማስቀም፣ ዕምቅ ግጭቶችን ለማምከን እና ዘላቂ አዎንታዊ ሰላምን ለማስፈን ይሰራል።

2.2.3.2 ፓርቲያችን ከህብረተሰብ ውስጥ የሚጀምር የሰላም እንቅስቃሴ ከየትኛውም መንግስታዊ ኃይል በላይ ሀገርን በሰላም የመምራት ታላቅ ጉልበት አለው ብሎ ያምናል። በመሆኑም ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ

እንዲቻል በህብረተሰቡ ውስጥ የግጭት ቀስቃሽ አስተሳሰቦችና ተግባራትን የሚጠየፍ ህዝባዊ ባህልን ለማዳበር በተቀናጀ መልኩ ይታገላል።

2.2.3.3 ፓርቲያችን ዘላቂ ሰላም የማረጋገጥ ግብ ከዴሞክራሲ፣ ከመልካም አስተዳደር እና ከልማት ፕሮግራሞቻችን ጋር በእጅጉ የተቆራኘ እንደሆነ ያምናል። በመሆኑም አዎንታዊ ሰላምን ለማረጋገጥ የልማት ስራዎችና ፍትሃዊነት ማረጋገጥ፣ ያልተማከለና አካታች የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት ብዝሃነትን ማክበር እንዲሁም የጋራ ህልምና ራዕይ በመፍጠር ለጋራ ዓላማ ስኬት በጋራ መንቀሳቀስ የሚያስችል የሀገረ-መንግስት ግንባታ ስራዎችን አቀናጅቶ በመስራት ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ ይሰራል።

2.2.3.4 የህግ እና የፍትህ ተቋማት ምንም እንኳን ተፈጥሯዊ ተግባራቸው የሆነውን ህግና ስርዓት ለማስፈን የሚያገለገሉ እንጂ ዜጎችን አፍኖ እና ጨቁኖ ለመግዛትና የገዥዎችን ጥቅምና ፍላጎት ለማስጠበቅ እንዳይውል ፓርቲያችን የህግና የፍትህ ተቋማት መሰረታዊ ዓላማ እና ተግባር የዜጎችን መሰረታዊ ነፃነት፣ መብት፣ እኩልነት በሚያከብር እና የጋራ ጥቅም፣ ማህበራዊ ፍትህ፣ ብልጽግና፣ ሰብአዊ ደህንነትን በሚያረጋገጥ መልኩ ህግና ስርዓትን ለማስፈን ይታገላል። የህግ ገዥነት መርሆች ማስከበር የሚያስችል እንዲሁም መንግስት ማህበራዊ እና ተቋማዊ የሆነ የህግ ገዥነት ባህል መፍጠር እንዲችል የሚያግዝ ንቁ የሆነ የህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲኖር ይታገላል።

2.2.3.5 ዘመናዊና ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በጣምራ በመጠቀም፣ ዕምቅ ግጭትን ማወቅ፤ የቅድመ ዝግጁነትና የምላሽ አቅምን በማዳበር ግጭትን ማምከን እና በትምህርትና በሚዲያ የታገዘ የህብረተሰብ ሰላማዊ ባህል በማዳበር ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ፓርቲያችን ይታገላል።

# ክፍል ሶስት

## III. የኢኮኖሚ ፕሮግራም

### 3.1 የኢኮኖሚ ፕሮግራም ዓላማ፡- ልማትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አካታች የኢኮኖሚ ስርዓት መገንባት

የብልጽግና ፓርቲ በኢኮኖሚ ፕሮግራሙ የህዝባችን ሰፊ ክፍል የሆነውን አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር፣ ወጣት፣ ሴቶች እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የከተማ

ነዋሪዎች ማዕከል ያደረገ አካታች የኢኮኖሚ ስርዓት በመገንባት የህዝባችንን የጋራ ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ዓላማ ይኖረዋል። ፓርቲያችን በሀገራችን ምርታማነትን እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ መንግስት ወሳኝ አቅምና መሣሪያ ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም የመንግስት በኢኮኖሚው ስርዓት ውስጥ ያለው ተሳትፎ የገበያ መርህን በመከተል ስትራቴጂካዊ በሆነ ሁኔታ ሀብት የሚፈጥር፣ በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ አስተዳደር ማህቀፍ ውስጥ የግሉን ዘርፍና ሌሎች የኢኮኖሚ ተዋናዮችን ተሳትፎ በማጎልበት ምርታማነትን በላቀ ደረጃና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚያሳድግ እንዲሆን ያደርጋል። በዚህም መሰረት ፓርቲያችን ጥራት ያለውና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት እንዲሁም ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋገጥ አረንጓዴ ኢኮኖሚ በመገንባት ሀገራችንን ወደ ብልጽግና ጎዳና ለማሸጋገር ያልማል።

## 3.2 የኢኮኖሚ ፕሮግራም ግቦች

### 3.2.1 የብዝሃ ዘርፍ የኢኮኖሚ መዋቅር መገንባት

3.2.1.1 በአንድ ክፍለ ኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ መዋቅር ዘላቂ ዕድገትንም ሆነ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን እንደማያረጋግጥ ፓርቲያችን ያምናል። ስለሆነም ሀገራችን አንፃራዊ ዕምቅ አቅሞችን ታሳቢ በማድርግ ከግብርና በተጨማሪ የኢንዱስትሪ እና ተዛማጅ የአገልግሎት ዘርፎችን በማሳደግ ኢኮኖሚያችን በብዝሃ ዘርፍ የተዋቀረና ዘላቂ ዕድገት ያለው እንዲሆን ይሰራል። ይህን ለማሳካት ፓርቲያችን ሀገራችን ዕምቅ ፀጋ የታደለችባቸው ክፍለ ኢኮኖሚዎችን በሙሉ አቅም አሟጦ ወደ ልማት የማስገባት የኢኮኖሚ አቅጣጫን ይከተላል።

3.2.1.2 ፓርቲያችን ሀገራችን ለግብርና ዘርፍ ያላትን የስነ-ምህዳር ተስማሚነት፣ የመሬት እና ሰፊ የሰው ሀብት በሙሉ አቅም ስራ ላይ እንዲውል በማድረግና የውሃ ሀብታችንን ማዕከል ያደረገ ልማትን ለማምጣት፣ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ የወጭ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ እና የገቢ ምግብ ነክ ሸቀጦችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት በትጋት ይሰራል። ይህም እንዲሆን ለማድረግ የግብርና ዘርፉ በግብአትና ቴክኖሎጂ አቅርቦት እንዲሁም አመራረትና የገበያ ትስስር መሰረት ያደረገ ግብርናን የማዘመን ስራ ይሰራል። ግብርናን በማዘመን ረገድ

የተቀናጀ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ የግብርና አሠራርን (Regenerative Agriculture) በማስፋፋት፣ አነስተኛ ይዞታ ላላቸው አርሶ አደሮች በቂና የተሟላ ግብአት እንዲቀርብ በማድረግ፣ የህብረት ስራ ማህበራትን በማጠናከርና በማስፋፋት፣ የገጠር ፋይናንስ ተደራሽነትን በማስፋት፣ የፋይናንስ ተቋማት ለግብርናው ዘርፍ በቂ ፋይናንስ እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ የመስኖ ልማት፣ ሜካናይዜሽን፣ የግብርና ማበረታቻ ስርዓት በመዘርጋት፤ የከተማ ግብርናን በማስፋፋት እና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ በማሳደግ ምርታማነትን ለመጨመር ይሰራል። ግብርናችን የአየር ንብረት ተጽዕኖን የሚቋቋም እንዲሆን የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እና የተራቆቱ አካባቢዎች በደን እንዲሸፈኑ ፓርቲያችን ይሰራል።

አርብቶ አደሩንና ከፊል አርብቶ አደሩን በሚኖርባቸው አካባቢዎች ያሉ የተፈጥሮ ፀጋዎች መሰረት በማድረግ ከህዝቡ የኑሮ ዘዬ ጋር የተጣጣመ የተቀናጀና ዘመናዊ የአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ-አደሮች አካባቢ ልማት በተለይም ዘመናዊ የእንስሳት እርባታና ልማት ፕሮግራም በመንደፍ ፓርቲያችን ለአርብቶ-አደር ህዝቦች ልማትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ይታገላል።

3.2.1.3 ኢንዱስትሪ የጠንካራና ዘመናዊ ኢኮኖሚ መሰረት እንደመሆኑ ዘርፉ በሀገራችን ኢኮኖሚ የሚሸፍነው ድርሻ እንዲሰፋ ፓርቲያችን በቁርጠኝነት ይሰራል። የኢንዱስትሪ ልማታችን ዋነኛ መርህ ኤክስፖርት መር ይሆናል። ሆኖም ግን ፓርቲያችን ሀገራችን የምታስገባቸውን የውጭ ሸቀጦች በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት ፖሊሲን የውጭ ንግዳችንን ከማሳደግ ጋር አስተሳስሮ ይተገብራል። ይህም እንዲሆን ዘርፉ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ጠንካራ የኋልዮሽና የፊትዮሽ ትስስር እንዲኖረው የሚያደርግ፣ ምርታማነት፣ ጥራት፣ ተወዳዳሪነትን የሚያሳድግ አቅጣጫን ይከተላል። የኢኮኖሚ ሽግግርን ለማፋጠን የግብርና እና ኢንዱስትሪ ዘርፉን ትስስር የሚያጠናክርና ሀገራችንን በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ቀዳሚ ማዕከል እንድትሆን የሚያስችል ስራዎችን በስፋት ይሰራል። ስለሆነም ዘርፉን ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ሳቢ፣ ትርፋማና አዳጊ ሊያደርጉ የሚችሉ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ፣ ምቹ የኢንቨስትመንትና ንግድ አካባቢን በመፍጠር እና የኢንዱስትሪ ሰላም በማስፈን ጠንካራ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ለመገንባት ፓርቲያችን

ይሰራል። ፓርቲያችን ግብርናን መሰረት ላደረጉ ኢንዱስትሪዎች፣ ለሰፊ የተማረ የሰው ኃይል ዘላቂና አስተማማኝ የስራ ዕድል የሚፈጥሩ እና በስፋት ገቢ ምርቶችን መተካት የሚያስችሉ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ የሚያደርግ አቅጣጫን ይከተላል።

3.2.1.4 ሀገራችን ያላትን የማዕድን ሀብት በልክ እና ቀጣዩን ትውልድ በማያራቁት መልኩ ለመጠቀም የማዕድን ጥናት፣ ፍለጋ እና ማውጣት እንዲሁም ለገበያ ማቅረብ ላይ ባለሀብቶች በተለይም የሀገር ውስጥ ባለ-ሀብቶች በተናጠልም ይሁን ከመንግስት ጋር በመተባበር እንዲሳተፉ ፓርቲያችን ሁኔታዎችን ያመቻቻል። የማዕድን ፍለጋ እና የማውጣት ስራ ዘመናዊ እና የአካባቢው ማህበረሰብ ላይ የደህንነት ስጋት የማይጥል እንዲሁም ከልማቱ ፍትሃዊ ተጠቃሚነቱንም የሚያረጋግጥ እንዲሆን ፓርቲያችን ይሰራል።

3.2.1.5 የአገልግሎት ዘርፍ በባህሪው በአንድ በኩል በራሱ እንደ ኢኮኖሚ ዘርፍ የስራ ዕድልና ሀብት የሚፈጥር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ከፍተኛ የሆነ የአስቻይነት ሚና ይጫወታል። በመሆኑም ፓርቲያችን ሀገራችን ከአገልግሎት ዘርፉ መንትያ የኢኮኖሚ ጥቅም ተጠቃሚ እንድትሆን ይሰራል። በዚህም ረገድ የቱሪዝም ዘርፉን በማልማት እና በማዘመን እንዲሁም የቱሪዝም አማራጮችን በማስፋት ሀገራችን በአፍሪካ ካሉ ዋና ዋና የቱሪስት መዳረሻዎች አንዷ እንድትሆን ፓርቲያችን ጠንክሮ ይሰራል። ይህንንም ለማድረግ የሀገራችንን ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ሰው ሰራሽ መስህቦችን የማስተዋወቅ እንዲሁም ለቱሪስት ፍሰትና ቆይታ ወሳኝ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚያሳድጉ እና ለቱሪስት ምቹ የሚያደርጉ፣ የቱሪዝሙን ዘርፍ የሚያዘምኑ ስራዎችን ነድፎ ይንቀሳቀሳል።

3.2.1.6 ፓርቲያችን የኢኮኖሚ ሴክተሮችን ውጤታማነትና ቅልጥፍና ለማሳደግ የሎጅስቲክስ እና መሰረተ ልማት አቅርቦትን በማሟላት ፈጣን፣ ውጤታማና ቀልጣፋ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴና ትስስር እንዲኖር ይሰራል። ሀገራችን የባህር በር አልባ በመሆኗ የሚያጋጥሙ የወደብ አገልግሎት ችግር ለመፍታት እንዲቻል ከጎረቤት ሀገራት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ ወጥ የሆኑ ስርዓቶች እንዲተገበሩ በማድረግ፣ የባህር ወደብን በጋራ የማልማት እንዲሁም አገልግሎት የመስጠት

ኢንቨስትመንቶች ላይ ተሳትፎ በማድረግ የሀገራችንን ጥቅም ለማስከበር ፓርቲያችን ይታገላል።

## 3.2.2 ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ልማት እና ምርታማነትን መሰረት ያደረገ ማህበራዊ ፍትህ ማረጋገጥ

3.2.2.1 የምናስመዘግበው የኢኮኖሚ ዕድገት ጠቅላላ ሀገራዊ ምርትን ከማሳደግ ባሻገር የህዝቦችን ሰብአዊ ልማት የሚያመጣ መሆን እንዳለበት ፓርቲያችን ያምናል። በመሆኑም ኢኮኖሚያችን ለሁሉም የኢኮኖሚ ተዋንያን ፍትሃዊ እና በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተመጣጣኝ የዕድገት ዕድልን የሚፈጥር፣ የዕድገት ምጣኔው እየሰፋና ግለቱን ጠብቆ የሚዘልቅ፣ ጥራቱን የጠበቀና በቀጣይ ትውልድ ኪሳራ ላይ የማይገነባ መሰረተ ጽኑ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ ፓርቲያችን ይሰራል።

3.2.2.2 ፓርቲያችን መንግስት መር ሆኖ የቆየውን ዕድገት ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚኖረውን ሚና አሁን ከሚገኝበት አነስተኛ ተሳትፎ ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ እንዲል በማድረግ አስፈላጊው ሁሉ ያደርጋል። የምናስመዘግበው የኢኮኖሚ ዕድገት ጥራት ያለው፣ የአካታችነት እና የዘላቂነት ችግሮችን የሚቀርፍ፣ ምርታማነትን የሚያረጋግጥ እንዲሁም ከከፍተኛ የዕዳ ጫና የተላቀቀ እና ጤናማ የፋይናንስ ሂደትን የተከተለ ኢኮኖሚያዊ ስርዓትን እንዲገነባ ይሰራል። በተጨማሪም አርሶና አርብቶ አደሮችን፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማ ነዋሪዎችን፣ ሴቶችና ወጣቶችን ከኢኮኖሚ ዕድገቱ በተጨባጭ ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን ይተገብራል።

3.2.2.3 ልማትን የሚያሳልጥና በየደረጃው ለህዝቡ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተደራሽ የሚሆን የኢኮኖሚና ማህበራዊ መሰረተ ልማት መኖር ለሀገራችን በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን ፓርቲያችን በጥብቅ ያምናል። በዚህም መሰረት በመንግስት፣ በመንግስትና በግል ባለሀብት ትብብር እና በግል ባለሀብት መዋዕለ ነዋይ፣ ጥራት ያላቸው መሰረተ ልማቶች እንዲገነቡና በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ህዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ፓርቲያችን በጥብቅ ይሰራል።

3.2.2.4 ፓርቲያችን በፌደራል ስርዓቱ ማዕቀፍ የበጀት ድልድል፣ የመሰረተ ልማትና የማህበራዊ ልማት ግንባታና ድልድል እንዲሁም ማንኛውም

የሀብት አጠቃቀም የሁሉንም ህዝቦች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ባረጋገጠ ሁኔታ እንዲፈጸም ይሰራል።

3.2.2.5 ፓርቲያችን ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ከአካባቢ ጋር የተስማሙና የብዝሃ-ህይወት ሚዛንን የጠበቁ እንዲሆኑ የሚያስችል የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ተግባራዊ ያደርጋል። በዚህም በተፈጥሮ ሀብት የታደለችው ሀገራችን በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ እንድትሆን የሚያደርጋትን የዝቅተኛ ካርቦን ልቀት እና የታዳሽ ኃይል ልማት ላይ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እንዲያድግ በማድረግ በሀገራችን የአረንጓዴ ኢኮኖሚ እንዲያብብ ይሰራል።

3.2.2.6 በሁሉም አካባቢዎች ያሉ የልማት ጸጋዎችን በማልማት እንዲሁም በአንፃራዊነት በልማት ወደ ኋላ ለቀሩ አካባቢዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት የተመጣጠነና ፍትሃዊ ልማት በሁሉም አካባቢዎች እንዲረጋገጥ ፓርቲያችን ይታገላል።

3.2.2.7 ፓርቲያችን በተለያዩ ሀገራትና ዓለም ክፍሎች ከሚፈጠሩ የኢኮኖሚ ቀውሶች የሚመጡ ጫናዎችን የሚቋቋም የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ እንዲሁም የኢኮኖሚ ነፃነት ያለው ሀገራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት ይሰራል። ይህንንም ለማድረግ ፓርቲያችን ሀገራዊ ፍላጎት እና አቅርቦትን ለማጣጣም ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል። ይህም ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ፣ ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚረዳ ሰፊ የገበያ ፍላጎትን መፍጠር ብሎም የኑሮ ውድነትን መቆጣጠር ላይ ያተኮረ ሆኖ ውጤታማ የማክሮ ኢኮኖሚ ትንበያ፣ የፖሊሲ ቀረፃ እና ማስፈጸም ላይ የሚያጠነጥን አቅም ግንባታ ላይ አተኩሮ ይሰራል።

3.2.2.8 የፋይናንስ ዘርፉ በቆጣቢ እና በኢንቨስተር የኢኮኖሚ አሃዶች መካከል የሚኖርን የገንዘብ መጠን ፍላጎት በማስታረቅ ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑን ፓርቲያችን በጽኑ ያምናል። ስለዚህም ዘመናዊ አሰራርና ተወዳዳሪነት የሰፈነበት መሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ የፋይናንስ ዘርፍ እንዲኖር ይታገላል። ይህም ሲሆን በሁሉም የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን አካታች የሆነ የፋይናንስ አገልግሎት በማስፋፋት እና ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ የዜጎችን የኢኮኖሚ አቅም ማጎልበት ላይ ትኩረት በማድረግ ይሰራል።

## 3.2.3 ሀብት ፈጠራን የሚያሳድግ ዕውቀት-መር ኢኮኖሚ መገንባት

3.2.3.1 ዘላቂ እና አስተማማኝ ብልጽግና የሚረጋገጠው ኢኮኖሚው ዕውቀትን እንደ ግብአትም ሆነ እንደ ምርት የሚጠቀም ሆኖ ሲገነባ እንደሆነ ፓርቲያችን ይገነዘባል። በመሆኑም በቴክኖሎጂ ዕድገት፣ በኢኖቬሽን እና በሰው ኃይል ልማት ላይ ያተኮረ የዕድገትና የልማት አቅጣጫ ከረጅምና መካከለኛ ጊዜ አኳያ መፈፀም ዋነኛ የፓርቲያችን ኢኮኖሚ ግብ አድርጎ ይንቀሳቀሳል።

3.2.3.2 በሀገራችን ቀጣይነት ላለው ምርታማነት እና የህዝብ ኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ቁልፍ የሆነው ዕውቀት እና ሳይንሳዊ ምርምር ዝቅተኛ ደረጃ በመሆኑ እንደሆነ ይገነዘባል። በመሆኑም ፓርቲያችን ዕውቀትን መሰረት ያደረገ ቴክኖሎጂ፣ የቢዝነስ ፈጠራ እንዲሁም በዘመናዊ የአመራርነት ክህሎቶች እና በተቋማት ግንባታ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያ ያደርጋል።

3.2.3.3 ፓርቲያችን ዕውቀት መር ኢኮኖሚ የሚገነባው ለሰው ኃይል ልማት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም ተወዳዳሪ፣ ምርታማና፣ ጤናማ የሰው ኃይል ልማት ላይ ትኩረት ያደርጋል። የኢኮኖሚውን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበና ገበያን መሰረት ያደረገ የሰው ኃይል ልማት ስትራቴጂን ተግባራዊ በማድረግ ብቁ እና ውጤታማ የሰው ኃይል በማልማት በዕውቀት የሚመራ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ፓርቲያችን ይሰራል።

## 3.2.4 ከተሜነት እና የከተማ ልማትን ማስፋፋት

3.2.4.1 ፓርቲያችን የገጠር ልማትንና የከተማ ልማትን በማቀናጀትና በማስተሳሰር ዜጎች በያሉበት በሀገራዊ ልማቱ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ እንዲሁም ከግብርና ልማት ወደ ኢንዱስትሪ ልማት የሚደረገው መዋቅራዊ ሽግግር እንዲፋጠን ከተሜነትን ለማስፋፋት ይታገላል። እንዲሁም የገጠር ማዕከላት፣ የገጠር ልማትንና የከተማ ልማትን በማስተሳሰር ለመዋቅራዊ ሽግግር አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይሰራል። የከተሞችን ሽፋን ዓለም-አቀፋዊ ስታንዳርዱን ጠብቆ የከተማው ነዋሪ ድርሻ ከገጠሩ የሚኖረው ምጥጥን ከፍ እንዲል ይሰራል።

3.2.4.2 ፓርቲያችን ከተሞች ጽዱ፣ ለኑሮ ምቹና አረንጓዴ እንዲሆኑ የተቀናጀ የከተማ ልማትን ፕሮግራም ነድፎ ይሰራል። ከተሞች የተቀናጀ የከተሞች መሰረተ ልማቶችን አቅርቦት እንዲያገኙ፣ ሞያዊ ብቃትን መሰረት ያደረገ ጠንካራ የከተማ አስተዳደር እና የፋይናንስ ስርዓት እንዲኖራቸው በማስቻል መሰረታዊ የሆኑ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ቀልጣፋ፣ ጥራት ያላቸው እና የህዝብን ፍላጎት የሚያረኩ እንዲሆኑ ፓርቲያችን ይሰራል።

3.2.4.3 ዘመናዊና የከተሞችን የዕድገት ሁኔታ ያገናዘበ የመሬት ልማትና አስተዳደር የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት የከተማ መሬት አቅርቦትንና አጠቃቀም ግልጽ፣ ልማትን የሚደግፍ እና ቀልጣፋ እንዲሆን ይደርጋል።

3.2.4.4 ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ በከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፤ በግል ዘርፍ ሰፊ ተሳትፎ የከተማ ቤት ልማትና አስተዳደር ስራዎችን ማጠናከርና የተቀናጀ የከተሞች መሰረተ ልማቶችን ያቀርባል።

3.2.4.5 ፓርቲያችን ከተሞችን ከከተሞች እንዲሁም ክልሎችን ከክልሎች በሚያዋስኑ ስፍራዎች በጥናት ላይ የተመሰረቱ የኢኮኖሚ ትስስርንና የልማት ኮሪደሮችን በማልማት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ይታገላል::

3.2.4.6 ለኢኮኖሚው ከፍተኛ ድርሻ ያለውን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትንና ህግጋትን እንዲሁም የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ መንገድ ዘርፉ በገበያው ተወዳዳሪ እንዲሆን እንዲሁም ሀገር በቀል ኩባንያዎች የሚጠናከሩበትን አሰራር በመተግበር ወደ ውጤታማነት እንዲሸጋገር ይሰራል።

3.2.4.7 ፓርቲያችን የዜጎች መሰረታዊ ፍላጎት የሆነውን የመጠለያ ጥያቄ ለማሟላት በተለይም በከተሞች ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ዜጎች ቤት የሚያገኙበት አሰራር፣ የመሬትና የፋይናንስ አቅርቦቶችን ይዘረጋል። በከተሞች የመኖሪያ ቤት ልማት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ አጋርነት፣ ወጪ ቆጣቢና ስፋት ያለው የቤት አቅርቦት በከተሞች እንዲኖርና የመሬት ፍጆታን በቀነሰና የወለል ከፍታን በሚጨምር መንገድ ተግባራዊ በማድረግ የቤት አቅርቦት ችግርን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ ይሰራል።

# ክፍል አራት

## IV. ማህበራዊ ፕሮግራም

### 4.1 የማህበራዊ ፕሮግራም ዓላማ፡- ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ አካታች ማህበራዊ ልማት

*ሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት መነሻዋ ዝቅተኛ ደረጃ በመሆኑ ሁለንተናዊ ማህበራዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ጉዳይ የፓርቲያችን ማህበራዊ ፕሮግራም አንድ ዋና ትኩረት ይሆናል። በመሆኑም የማህበራዊ ልማት ስራዎቻችን የዕድገትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት መንትያ ግቦችን የማሳካት ጉዳይ ይሆናል። የማህበራዊ ልማት ስራዎቻችን ከችሮታና ከነባሩ የማህበራዊ ደህንነት ትኩረት ወጥቶ ችግሩን ከመብት አንፃር የሚመለከተው ይሆናል። ማህበራዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚደረገው ጥረት ተደራሽነትና አካታችነት ባለው መልኩ የማህበረሰብን ጤና፣ ደህንነት እና ምቾት የሚያስጠብቅ መሆን ይኖርበታል። የማህበራዊ ፕሮግራማችን ዜጎችን የሚያስተሳስር፣ ከችግርና ከመከራ የሚታደጋቸው፣ የሀገርን አለኝታነት የሚያሰርጽ እና በሀገራችን አዎንታዊ ሰላምን የሚያረጋግጥ ይሆናል። የማህበራዊ ልማት ፕሮግራማችን ህብረ-ብሔራዊ ማንነትን መሰረት ያደረገ ሀገራዊ አንድነትን የሚያጎለብት እንዲሆን ዒላማ አድርጎ መንቀሳቀስ የፓርቲያችን የማህበራዊ ፕሮግራም ዓላማ መገለጫ ይሆናል። ይህንንም እውን ለማድረግ በማህበራዊ ልማት ዘርፍ የአርሶ አደሩን እና አርብቶ አደሩንና ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የከተማ ነዋሪ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንዲሁም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የዜጎች አገራዊ አገልግሎት እንዲስፋፋ ፓርቲያችን ይሰራል።*

### 4.2 የማህበራዊ ፕሮግራም ግቦች

#### 4.2.1 ፍትሃዊነት፣ ጥራት እና አግባብነት ያለው የትምህርትና ስልጠና ስርዓት ማረጋገጥ

4.2.1.1 *በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ጨምሮ የትምህርትና ስልጠና ተደራሽነትና ፍትሃዊነት ለማስፋት እንዲሁም መሃይምነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ ፓርቲያችን ይታገላል፡፡ በዚህም መሰረት የቅድመ-መደበኛና መደበኛ ትምህርት በሀገራችን ሙሉ ለሙሉ እንዲዳረስ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ ቢሆንም ትኩረት ሳይሰጠው*

የቀረውን የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ለማሳደግ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፡፡

4.2.1.2 ፓርቲያችን በዋናነት የትምህርት ተደራሽነትን አስጠብቆ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የትምህርት ጥራትን ማሳደግ የትምህርት ፕሮግራሙ ዋነኛ አላማ አድርጎ ይታገላል፡፡ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የትምህርት ተቋማት በቁሳቁስና ቴክኖሎጂ የተደራጁ እንዲሆኑ እንዲሁም መምህራን በተሻለ ችሎታና ስነ-ምግባር የታነፁ ሆነው ትውልድን በእውቀት እና በስነ-ምግባር ቀራጮች እንዲሆኑ እንዲሁም የሚገባቸውን ክብርና ጥቅም እንዲያገኙ ፓርቲያችን ይሰራል፡፡

4.2.1.3 የሀገራችን ከፍተኛ ትምህርት ከኢንዱስትሪው የሰው ኃይልና የምርምር ፍላጎት ጋር ያለውን ትስስርና አግባብነት ያለው እንዲሆን ፓርቲያችን ይሰራል። የከፍተኛ ትምህርት ቅበላ ስርዓቱ የተማሪዎችን ፍላጎትና ዝግጁነት ግምት ውስጥ በማስገባት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎትና አቅምን ባገናዘበ መልኩ እንዲቀረጽ ያደርጋል። በተጨማሪም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዕውቀትና የጥበብ መናኸሪያዎች፣ ብዝሃነትን የሚያጎለብቱና እርስ በእርስ መቀራረብን የሚፈጥሩ የዓለም አቀፋዊ ዕሴቶችና አስተሳሰቦች ማዕከላት እንዲሆኑ ፓርቲያችን አበክሮ ይሰራል።

4.2.1.4 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ አቅማቸው እንዲጎለብት ተደርጎ ለኢንዱስትሪው የጀርባ አጥንት የሆነ ብቃት ያለው የሰው ሀይል እንዲያመርቱ ከማድረግ ባሻገር ለቴክኖሎጂ ሽግግር ሚናው ከፍ ያለ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

4.2.1.5 ፓርቲያችን በመጀመሪያ እርከን የትምህርት ቋንቋ ብዝሃ ልሳን እንዲሆን የሚያደርግ ሲሆን ብዝሃ ልሳንነቱ የምንገነባውን ህብረ-ብሔራዊ አንድነትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከክልሎች ነባራዊ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።

4.2.1.6 የግብረ-ገብ እና ስነ-ዜጋ ትምህርት አብሮነትን በማሳደግና ግብረ ገባዊ ዕሴቶችን በማስፋትና በማስረጽ እንዲሁም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የዜጎች አገራዊ አገልግሎት በመልካም ስነ-ምግባር የታነፀ ሀገር ወዳድ ትውልድ በማፍራት ረገድ የሚጫወተው ሚና እጅግ የላቀ እንደሆነ ፓርቲያችን ይረዳል። ስለዚህ የግብረ-ገብና ስነ-ዜጋ ትምህርት እንዲሁም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የዜጎች አገራዊ አገልግሎት ህብረ-ብሔራዊ ወንድማማችነትንና እህትማማችነትን የሚያጠናክር፣ የሀገር ፍቅርንና

አርበኝነትን የሚያፀና እና ግብረ-ገብነትን የተላበሰ ትውልድ መፍጠሪያ ተደርጎ እንዲቀረጽ ያደርጋል።

4.2.1.7 ፓርቲያችን ሁሉም የትምህርት ተቋማት የአካዳሚ ነፃነትን ከሚያቀጭጩ እና በዕለት ተዕለት የመማር ማስተማር፣ የምርምር ስራ ከፖለቲካዊም ሆነ ከአስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነቶች ነፃ እንዲሆኑ በማድረግ፣ ሁሉም ዕይታዎች በእኩል መድረክ አግኝተው በነፃነት የሚንሸራሸሩባቸው እንዲሆኑ ይሰራል።

## 4.2.2 መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ስርዓት መዘርጋት

4.2.2.1 ፓርቲያችን በዋናነት በሽታን በመከላከል ላይ የተመሰረተ የጤና ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል። በተጨማሪም አክሞ የማዳን አቅምን በዘላቂነት ለማሳደግ የሰው ኃይል፣ ስርዓትና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ላይ ፓርቲያችን ቅድሚያ ይሰጣል።

4.2.2.2 ፓርቲያችን ለእናቶችና ህፃናት ጤና እንክብካቤ ልዩ ትኩረት በመስጠት ይሰራል፡፡ የሴቶች ጤና የስነ-ተዋልዶ ጤና ችግር ለመቅረፍ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱ እና አጠቃላይ የሴቶችን ጤና ለመጠበቅ ከቅድመ ወሊድ እስከ ድህረ ወሊድ ድረስ በአቅራቢያቸው በጤና ተቋማት አገልግሎት እንዲያገኙ ፓርቲያችን ይታገላል። ሀገራችን በጤና ዘርፍ ወደ ኋላ የቀረችባቸውን ዘርፎች አንዱ የሆነው የጨቅላ ህፃናት ጤና እንክብካቤ ትኩረት እንዲሰጠው ይሰራል።

4.2.2.3 በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ያሉ ዜጎችን ታሳቢ ያደረገ የህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት አሰራር እንዲዘረጋ ያደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ የጤና መድህን ሽፋን በመላ ሀገራችን እንዲዳረስ አሰራርን በማዘመን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ደረጃውን የጠበቀ የጤና መድህን ሽፋን ተጠቃሚ እንዲሆን ያደረጋል።

4.2.2.4 ፓርቲያችን ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና የስነ-ህዝብ ፓሊሲ መሰረት ነው ብሎ ያምናል። ፓርቲያችን የህዝብ ቁጥሩ ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገታችን ጋር ተመጣጥኖ እንዲሄድ እንዲሁም ጤናማ የሆነ ህብረተሰብ ለመፍጠር የሚያስችል በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የቤተሰብ ምጣኔ ፕሮግራሞች እንዲዘረጉ ያደርጋል።

4.2.2.5 የህክምና ባለሙያዎች ፍልሰትን በተለይም ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ የባለሙያዎችን ፍልሰት ለመቀነስ በገጠር የሚሰሩ ባለሙያዎችን ልዩ ጥቅምን ይሰጣል።

4.2.2.6 የህክምና ቁሳቁስ እጥረትን ለመቀነስ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል። የህክምና ቁሳቁሶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚደረግበት አቅም እንዲፈጠር ፓርቲያችን ይሰራል።

4.2.2.7 የባህል ህክምና እንዲዘምን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከዘመናዊ ህክምና ጋር እንዲደጋገፍና በጥናትና ምርምር እንዲልቅ ያደረጋል።

## 4.2.3 የሀገራችንን አቅም ያገናዘበ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት መዘርጋት

4.2.3.1 የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓታችን ህዝባችንን ከአስከፊ ችግርና ከጉስቁልና ኑሮ በመጠበቅ ጤናማ ማህበረሰባዊ መስተጋብር እንዲኖር ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ ያደርጋል። ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመደገፍ የሀገራችን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና አቅም ያገናዘበ፣ አካታችና ጥራታቸውን የጠበቁ የማህበራዊ ዋስትና ስርዓቶችን ፓርቲያችን እንዲዘረጋ ይደረጋል።

4.2.3.2 የአካል ጉዳተኞችን ሁለንተናዊ መብት፣ ክብርና ደህንነት ለማስጠበቅ እንዲሁም በሁሉም የህይወት ዘርፎች ተሳትፏቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ በሙሉ ቁርጠኝነት ይሰራል። የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በተሻለ ሁኔታ በመምራት አካል ጉዳተኞች እንደ ማንኛውም ዜጋ በሀገራቸው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሰራል።

4.2.3.3 ፓርቲያችን አሰሪና ሰራተኛ በስራ ቦታ ጤናማ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው፣ የስራ ቦታዎች ምቹና ጤናማ እንዲሆኑ እና የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ይሰራል። ሰራተኛው ከኢንዱስትሪው ምርታማነት ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆንና በነፃነት ተደራጅቶ የመንቀሳቀስ መብቱ ሙሉ ለሙሉ እንዲከበርለት እና አሰሪውም ተገቢ ጥበቃ እንዲያገኝ ይደረጋል።

## 4.2.4 የሴቶችንና የወጣቶች የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማጎልበት

4.2.4.1 ሴቶችና ወጣቶች በሚደርስባቸው ሁለንተናዊ ጭቆና ምክንያት የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የፖለቲካ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸው አሁንም በሚፈለገው ልክ አለመሆኑ ፓርቲያችን ይረዳል። በመሆኑም የሴቶችና ወጣቶች ፍትሃዊ ማህበራዊና የፖለቲካ ውክልናና ተሳትፎ እንዲሁም ዘላቂ የስራ ዕድል፣ የብድር አቅርቦት፣ የመሬት ባለቤትነት፣ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚነት እና ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ እንዲያገኙ ፓርቲያችን ይታገላል።

4.2.4.2 ፓርቲያችን አጠቃላይ ኢኮኖሚና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎቻችን ወጣቱን ማዕከል ያደረጉ እንዲሆኑ ይሰራል። ወጣቶች በተማሩት የትምህርት ደረጃ፣ ባላቸው ዕውቀት፣ እንዲሁም በጥናት አዋጪ በሆኑ ዘርፎች ላይ እንዲሰማሩና ውጤታማ እንዲሆኑ ሰፋፊ የስራ ዕድል አማራጮችና ዕድሎች እንዲፈጠሩ ፓርቲያችን ይሰራል። የወጣቶችን የስፖርት ማዘውተሪያዎችና የመዝናኛ ስፍራዎችን በጥራትና በብዛት በማሳደግ ወጣቶች ንቁና ግብረ-ገብነትን የተላበሱ እንዲሆኑ እንዲሁም ከሱስና ከጥፋት የራቁ እንዲሆኑ ፓርቲያችን ይሰራል።

4.2.4.3 ፓርቲያችን የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት በህግ እና በተቋም ታግዞ ዜጎች ለተገቢ አገልግሎት ተገቢ ክፍያ እንዲያገኙ ክትትል እና ድርድር በማድረግ የዜጎች ደህንነት እና ክብር እንዲጠበቅ ይታገላል።

## 4.2.5 ብዝሃነታችንን ማዕከል ያደረገ የቋንቋ፣ ባህልና ቅርስ ልማት

4.2.5.1 ህብረ-ብሔራዊ ሀገር የመፍጠር ትልምን እውን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ የሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋዎች እንዲያድጉና እንዲጎለብቱ የህግ፣ ተቋማዊ እና አስተዳደራዊ ስራዎች ተግባራዊ ያደርጋል። የኢትዮጵያን ብዝሃነትን በሚገልጽ መልኩ ተጨማሪ የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋዎች ስራ ላይ እንዲውሉ ፓርቲያችን ይታገላል።

4.2.5.2 ፓርቲያችን የኢትዮጵያዊ የጋራ ዕሴቶችና ባህሎች እንዲጎለብቱ፣ ታሪካዊ ቅርሶቻችን፣ የሚዳሰሱም ሆነ የማይዳሰሱ ባህላዊና ትውፊታዊ ቅርሶቻችን ተገቢው ክብርና ትኩረት ተሰጥቷቸው፣ ከአደጋ ተጠብቀው ለሀገር ግንባታ

መሣሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ እና ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፉ በትኩረት ይሰራል። ፓርቲያችን የቀደሙ ቅርሶችን ከመጠበቅ ባሻገር ዘመን ተሻጋሪ የትውልድ አሻራና ቅርስ ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ አበክሮ ይሰራል።

4.2.5.3 ፓርቲያችን ስፖርት ሀገራዊ ክብርን እና ሀገራዊ መቀራረብን የሚያረጋግጥ የብልጽግና አንድ አካል እንደሆነ በመረዳት **"ስፖርት ለሁሉም"** በሚል መርህ ሀገራዊ አንድነትንና የህዝቦችን ወንድማማችነትና እህትማማችነት ለማጠናከር ስፖርት ተቋማዊና ህዝባዊ እንዲሆን ይሰራል።

4.2.5.4 ኪነ-ጥበብ በዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነቱ ጎልብቶ የሀገራችን ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ቀጠናዊ ተጽዕኖ የመፍጠሪያ ኃይል እንዲሆን እንዲሁም ኪነ-ጥበብ ለህዝቦች መተዋወቅ፣ መቀራረብ፣ መግባባትና ለአንድ ሀገራዊ ዓላማ መቆም ጠቃሚ እንደሆነ ፓርቲያችን ይገነዘባል። በመሆኑም ኪነ- ጥበብ የማህበረሰቡን ጠቃሚ ዕሴቶች ለማጎልበት ተገቢውን ሚና እንዲወጣ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ኪነ-ጥበባዊ ሀብት በትምህርትና ስልጠና እንዲታገዝ፣ የኪነ-ጥበብ ተቋማትና ማዕከላት ተስፋፍተው ለሀገር ብልጽግና እንዲውሉ ይታገላል።

# ክፍል አምስት

## V. የውጭ ግንኙነት ፕሮግራም

### 5.1 የውጭ ግንኙነት ዋና ዓላማ፡- ሀገራዊ ክብርን ማዕከል ያደረገ የውጭ ግንኙነት

ፓርቲያችን የውጭ ጉዳይን ከሀገር ውስጥ ጉዳይ የተነጠለ አድርጎ አይመለከትም። ይልቁንም የሀገር ውስጥ ጉዳያችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች ነፀብራቅ ሆኖ ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን ያልዘነጋ ነው። የውጭ ግንኙነታችንም የዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ግንባታን የሚያረጋግጥ፤ የሀገር አንድነትን በማስጠበቅ ሀገራዊ ክብርን የሚያጎናጽፍ፤ ሀገራዊ ክብርን በማጎናጸፍ ሀገራዊ አንድነትን የሚያጠናክር ይሆናል። ሀገራዊ ክብር የሌለው ሀገር ሀገራዊ ጥቅሙን ሊያስጠብቅ እንደማይችል ፓርቲያችን በጥብቅ ይገነዘባል። በመሆኑም የኢትዮጵያን ታሪክ እና አንድነት እንዲሁም የዜጎቿን ክብርና ተስፋዋን የሚያንፀባርቅ የጋራ ስምምነት ያለው ሀገራዊ ክብርን እና ሀገራዊ ጥቅማችንን የሚያስጠብቅ የተቀናጀና የተማከለ

የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ትግበራን እውን ያደርጋል። ሀገራዊ ክብራችንን ለማረጋገጥ እና ጥቅሞቻችንን ለማስከበር፣ አስቀድሞ ግንኙነትን በማደስና በማጠናከር ላይ ያተኮሩ ስራዎችን መስራት ላይ ትኩረት በማድረግ በግንኙነት ብልሽት ምክንያት የምናጣቸውን ሀገራዊ ጥቅሞቻችንን ለማስከበር አመች ሁኔታ ይፈጥራል። በውጭ ግንኙነት መስክ ሀገራችን መልካም የሚባል ውጤት ያስመዘገበች ሀገር ብትሆንም የውጭ ግንኙነታችን ከጉድለት እና ከግድፈት የፀዳ አይደለም። ስለዚህ ግድፍቶቹን እና ጉድለቶችን መለየት፣ ማስተካከል እና መሙላት እንዲሁም የነበሩ ጠንካራ ጎኖችን ማስቀጠል የፓርቲያችን የውጭ ግንኙነት መሰረቶች ናቸው።

## 5.2 የውጭ ግንኙነት ግቦች

### 5.2.1 ሀገራዊ ክብርን የሚያረጋግጥ የውጭ ግንኙነት

5.2.1.1 ፓርቲያችን የዜጎቻችን ክብር የሀገራዊ ክብራችን ዓይነተኛ መገለጫ እንደሆነ ይገነዘባል። በመሆኑም ዜጎቻችን በየትኛውም የዓለም ክፍል ቢሆኑ ክብራቸውን የሚያስጠብቅ የውጭ ግንኙነት ስራ የፓርቲያችን የውጭ ግንኙነት መርሃ-ግብር ቁልፍ መርህ ነው። ፓርቲያችን የዜጎችን ክብር መሰረት ያደረገ ሀገራዊ ክብርን ለማስጠበቅ ዜጎችን መሰረት ያደረገና የዜጎችን መብት በየትኛውም የዓለም ክፍል ሊያስጠብቅ የሚችል የውጭ ግንኙነት ስራዎችን ይተገብራል።

5.2.1.2 ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍላት ስራ ፍለጋ ይሰደዳሉ። በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ለስራ የወጡ ዜጎቻችንን ደህንነት፣ ክብር እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ታሳቢ ያላደረገ የውጭ ግንኙነት የኢትዮጵያን ክብር ሊያስጠብቅ ስለማይችል ፓርቲያችን በውጭ ግንኙነት እነዚህን ዜጎቻችንን ታሳቢ ያደረገ ስራን ይሰራል። የሀገራችን ዜጎች ከውጭ የስራ ቅጥር የተሻለ ተጠቃሚ የሚሆኑበት እና መብቶቻቸውና ክብራቸው የሚጠበቅበት ሁኔታ ከቀጣሪ መንግስታት ጋር ስምምነትን በመፍጠር እንዲመቻች ያደረጋል።

5.2.1.3 የሀገራችንን መልካም ገጽታና የወደፊት ብሩህ ተስፋ ለውጭው ዓለም የሚያስተዋውቁ የውጭ ግንኙነት ስራዎች ይሰራሉ።

5.2.1.4 የፓን-አፍሪካኒዝም መሰረት የሆነችው ሀገራችን መላው ጥቁር ህዝቦች የሚያከብሩትና የሚያምኑትን ያህል ፓን-አፍሪካኒዝምን የሚያጠናክር

የውጭ ግንኙነት ስራዎችን መተግበር ይኖርባታል። ፓርቲያችን ይህን በመረዳት የፓን-አፍሪካኒዝም መሰረትነታችንን የሚያጎሉ ስራዎች እንዲተገበሩ ያደርጋል።

## 5.2.2 ለትብብርና ለጋራ ተጠቃሚነት ትኩረት በመስጠት አጋሮቻችንን ማስፋት

5.2.2.1 ፓርቲያችን የተሻለው መንገድ በትብብርና ፉክክር መሃል ሚዛን መጠበቅ እንጅ ያልተገባ ፉክክር ተገቢ እንዳልሆነ በማመን የውጭ ግንኙነታችን ፖሊሲና ትግበራ ትብብርን፣ የጋራ ጥቅምን እና ሉዓላዊነትን በማስከበር እና በማክበር ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ያምናል። ችግሮችን ለመፍታትም ሆነ ሀገራዊ ጥቅምን ለማስከበር ቀዳሚው ነገር ግንኙነትን ማደስ እንደሆነ ያምናል። በመሆኑም በፉክክር እና በመቀናቀን ከሚመጣ አንፃራዊ ጥቅም ይልቅ ከውስጣዊ ፍላጎታችን የሚመነጭ ጥቅምን የሚያስቀድም የውጭ ግንኙነት በመከተል አጋሮቻችን ለማስፋትና ግንኙነትን ለማጠንከር አበክሮ ይሰራል።

5.2.2.2 የምንኖርበት ዓለም ባለ ብዙ ዋልታ እንደመሆኑ ከየትኛውም ዋልታ ዲፕሎማሲያዊ ጥግ ሳንይዝ በዋልታዎች መካከል ዲፕሎማሲያዊ ሚዛንን በመጠበቅ ሀገራዊ ጥቅማችንን ለማስከበር ይሰራል። ዲፕሎማሲያዊ ሚዛንን በመጠበቅ ከነባር አጋሮች ጋር የነበረ ግንኙነት እንዲጠናከር ከመስራት ባሻገር ከአዳዲስ አጋሮች ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ይደረጋሉ።

## 5.2.3 የብዙዮሽ ትብብር ተቋማት ተሰሚነትን መጨመር እና ፓሊሲያዊ ነፃነትን ማስከበር

5.2.3.1 የብዙዮሽ ዲፕሎማሲን በመጠቀም ዓለም አቀፍ ተሰሚነታችንን ማሳደግ እና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ሉዓላዊነታችንን የጠበቀ መልካም ግንኙነትን መፍጠር ላይ ፓርቲያችን ይሰራል። የፖሊሲ ነፃነታችንንና ሉዓላዊነታችንን ባስጠበቀ መልኩ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የባለ ብዙዮሽ ትብብርን ለማጠናከር የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራል። ፓርቲያችን ሀገራችን በብዙዮሽ ዲፕሎማሲ የአፍሪካ ድምጽ በመሆን የተባበሩት

መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባል እንድትሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል።

### 5.2.4 ለጎረቤት ሀገራት ትኩረት በመስጠት ዘርፈ ብዙ የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

5.2.4.1 ሀገራችን ከጎረቤት ሀገራት ጋር በመተባበርና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ግንኙነት በመፍጠር አካባቢያዊ ሰላም እንዲረጋገጥ ፓርቲያችን በትኩረት ይሰራል። የአካባቢያዊ ሰላም ችግር የሆኑ ሽብርተኝነትና ሌሎችም የሰላም ጠንቅ የሆኑ ጉዳዮችን ለመግታት ከጎረቤትና ሌሎች ሰላም ወዳድ ሀገራት ጋር በመሆን በቅንጅት ይሰራል። በተጨማሪም ለአካባቢያዊ ሰላም መደፍረስ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ በጎረቤት ሀገራት መካከል ያሉ መልካም ያልሆኑ ግንኙነቶች እንዲሁም በጎረቤት ሀገራት ውስጥ ያሉ አለመግባባቶች ቀጣናዊ ችግሮችን ከመፍጠራቸው በፊት በሰላማዊ መልኩ መግባባት እንዲፈጠርባቸው የማግባባት ስራዎች ይሰራል።

5.2.4.2 በቀጣናው ካሉ ሀገሮች ጋር የጋራ ጥቅሞቻችንን መሰረት ያደረገ አካባቢያዊ የልማት፣ የኢኮኖሚ እና የሰላም ትስስር እንዲፈጠር በትብብር ይሰራል። ይህም ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድ ቀጣናዊ የኢኮኖሚ ትስስር እንዲሆን አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል። ይህንንም ለማድረግ በቀጣናችን ያሉ ነባር አካባቢያዊ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ ለማድረግ እንዲሁም ድርጅቶቹ ለቀጣናዊ ትስስር መፈጠር መሰረት እንዲጥሉ በትኩረት ይሰራል። በተጨማሪም እነዚህ አካባቢያዊ ድርጅቶች የቀጣናው የተበታተኑ ድምፆች ወደ አንድ መሰባሰቢያ በማድረግ የቀጣናው ሀገራት የመደራደሪያ አቅም እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል።

5.2.4.3 ከጎረቤቶቻችን ጋር በሚያገናኙን የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ በጋራና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት መርህ የሀገራችንን ጥቅም ለማስከበር ፓርቲው ይሰራል። ድንበር ተሻጋሪ ወንዞቻችንን የመጠቀም መብታችንን ባከበረ፣ ዓለም አቀፍ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች መርሆችን በተንተራሰ መልኩ ለጥቅም እንዲውሉ ይደረጋል። እንዲሁም በአጠቃቀም ምክንያት የሚመጡ አለመግባባቶችም በዓለም አቀፍ መርሆችና በዲፕሎማሲያዊ መንገዶች እንዲፈቱ በዘላቂነትም በወንዞቹ ላይ ሁሉን አቀፍ የሆነ ስምምነት

እንዲደረስ ያደርጋል። በተመሳሳይ ሀገራችን በአካባቢያችን ካሉ ባለ ወደብ ሀገሮች የተሻለ የወደብ ተጠቃሚነት መብት በሚያረጋግጥ መልኩ አካባቢያዊ ትብብሮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ ያደርጋል።

## 5.2.5 የኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ተሳትፎ ማሳደግ

5.2.5.1 ከሀገራቸው ጋር የተለየ ቁርኝት ያላቸው በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከሀገራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎች የተነጠሉ እንዳይሆኑና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። በዚህ ጉዳይ ኤምባሲዎቻችን ከምንም ጊዜ በላይ በውጪ ላሉ ዜጎች እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቅርብ ይሆናሉ። ለመብቶቻቸው ቀድሞ ደራሽና ጠበቃ፣ ለደህንነታቸው ቀዳሚ ዋስትና እንዲሆኑ ይደረጋል።

5.2.5.2 በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ጉዳይ ላይ ባለቤት እንዲሆኑ ከሚደረገው ጥረት ባሻገር በየሚኖሩበት ሀገር የኢትዮጵያ አምባሳደሮች እንዲሆኑ በማበረታታት ላይ በትኩረት ይሰራል

## 5.2.6 ሀገራዊ ክብርን እና ሀገራዊ ጥቅምን የሚያስጠብቅ የውጭ ግንኙነት የመፈፀም አቅም መገንባት

5.2.7.1 ፓርቲያችን የኢትዮጵያን ታሪክ እና አንድነት እንዲሁም የዜጎቿን ክብር እና ተስፋዋን የሚያንፀባርቅ የጋራ ስምምነት ያለው ሀገራዊ ክብራችንን እና ሀገራዊ ጥቅማችንን የሚያስጠብቅ የተቀናጀ እና የተማከለ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ትግበራ እውን ያደርጋል። የውጭ ግንኙነት ተቋሞቻችን የውጭ ግንኙነትን የማስፈፀም አቅማቸው የላቀ እንዲሆን የመምራት አቅም ባላቸው አመራሮችና የመፈጸም ብቃት ባላቸው ባለሞያዎች እንዲዋቀሩ ያደረጋል። አምባሳደሮቻችን የሀገራችንን ስምና ክብር እና የኢትዮጵያን አንድነት የሚያንፀባርቁ መሆን እንዳለባቸው ፓርቲያችን ያምናል። በመሆኑም አምባሳደሮች ሀገራችንን እና ታሪኳን ጠንቅቀው የሚያውቁ እና ሀገራዊ ክብራችንን የሚያስጠብቁ፣ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ዕውቀት ያላቸው እንዲሆኑ ይደረጋል። በተጨማሪም የውጭ ግንኙነት ዘርፉና ተቋማት ወቅቱን ባገናዘበ ሀገራዊ ሁኔታዎች እና ዓለም

አቀፍ ዕድገቶች በተቃኘ መልኩ እንዲያድጉ እና እየተለወጡ እንዲመጡ ይሰራል።

5.2.7.2 ፓርቲያችን የውጭ ግንኙነት ማስፈፀሚያ ሀገራዊ አቅማችን በሀገር ኃይል አቅማችን ላይ እንዲመሰረት ሰፊ ጥረት ያደርጋል። ይህም ካለን ወረት በተጨማሪ በቀጣይ በሚከናወኑ የመልካም ገጽታና አዎንታዊ ተጽዕኖ የመፍጠሪያ ተግባራት በመነሳት እየተገነባ የሚሄድና በጎረቤቶቻችንም ሆነ ከሌሎች ሀገራት ጋር በምንፈጥረው መተማመን ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እየዳበረ የሚሄድ ይሆናል። ለዚህም በህዝብ ለህዝብ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

5.2.7.3 የሀገራዊ ሉዓላዊነትን የማስጠበቅ ጉዳይ በሀገር ኃይሎች አቅም ብቻ የሚመለስ ባለመሆኑ ሀገራዊ ክብራችን ሳይደፈር የመግታት አቅም ያለው ጠንካራ፣ ዘመናዊና ሁሉን አቀፍ ወታደራዊ ኃይል መገንባት ይገባል ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። በመሆኑም የመከላከያ አቅማችን የዘመኑን አውደ ውጊያ የዋጀ፣ በዋናነት ጥቃትን ከወዲሁ የማስቀረት አቅምን መሰረት የሚያደርግ፣ በማንኛውም መስክ የሚቃጡትን ትንኮሳዎች መመከት የሚችል፣ ለዜጎቻችን ኩራት በሚሆንና ሀገራዊ ጥቅማችንን በሚያስጠብቅ መልኩ እንዲደራጅ ይሰራል።

5.2.7.4 ፓርቲያችን ሀገራዊ ክብራችንን እና ሀገራዊ ጥቅማችንን ሊያስከብር የሚችል ዘርፈ ብዙ ዲፕሎማሲን የመተግበር አቅማችንን ማሳደግ እና ከመተግበር ላይ ትኩረት ያደርጋል። ሁሉን አቀፍ ዲፕሎማሲን በመተግበር የትብብር ዘርፎችን ማስፋት ፓርቲያችን ቅድሚያ ሰጥቶ ይሰራል። በዚህም የሰላም፣ የኢኮኖሚ፣ የዜጋ-ተኮር እና ፐብሊክ ዲፕሎማሲ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዋነኛ መተግበሪያ ስትራቴጂ ሆነው እንዲሰራባቸው ትኩረት ይሰጣል። በሌላ በኩልም ለመገንባት ለምንጥረው እውቀት መር ኢኮኖሚ እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ከሚፈለገው የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ፣ ብሎም ከቀደሙት ሀገራት ልምድን ለመቅሰምና የዕውቀት ሽግግር ለማድረግ የሳይንስ ዲፕሎማሲን የሚያጠናክሩ ስራዎች ይሰራሉ።

**መጋቢት 2014 ዓ.ም**
**ብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና)**
**አዲስ አበባ**